## መዘክር

### እነማን ነበሩ

ባቡር ጉዞውን ሲጀምር ሲንቀሳቀስ
ተሳፋሪ መንገደኛው ሸኚው ሁሉ
ሲተራመስ፣
እርስበርስ መጠራራት
አተካሮ ውካታ ወይም ወሬ ማውራት፣
የድምፅ ብዛት ሲያስተጋባ
ሞተር ሲፋጭ ሲያጉረመርም
የሰው ልጅ አቅም አጥቶ
እየተጣደፈ ሲገባ፣
ሩጫ ችኮላና መራኮቱ ሲያስገርም።

ያነሳውን አንስቶ የጣለውንም ጥሎ
በረራ በረራ ግስጋሴውን ሲቀጥል
አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ፣
ረጋ ብሎ ቢሄድስ ምናለ
ለሁሉም እኩል ሳያዳላ ባስተዋለ
ባቡር መንገዱን በጠራ ስልት በቀጠለ።

እነማን ነበሩ ቆመው የሚያዩትስ
ሲታዘቡት
አረህ ላረህ ሲጋልብ ሲሮጥ ያስተዋሉት፣
ሕግ ሥርዓትና ደንብ በሌለበት አገሩ
እንዳሻው በፍጥነት ሲበር ባቡሩ፣
ምግባሩን ሁሉ እንደመልካም የቀሰሙት
እነማን ይሆኑ በቅርቡ ሆነው የተማሩት።

ኑና ሁላችንም በአንድነት ሆነን
ተኮልኩለን
የአጉል ባሕል ልምድ እንዳይሰፍን
ተሰልፈን
ባቡሩ የጫነውን ሁሉ ከእናካቴው
አስወርደን፣
ጥላቻ ግለኝነት ቅጥፈት ሌብነትን
እናጥፋቸው
ከባቡሩ ሸቀጥ ጋር አብረው ከወረዱ
ኋላ ለመጪው ትውልድ ጠንቅ ናቸው።

እነማን ነበሩ አብረው በባቡሩ የተጓዙት
ነጂው ሲሳሳት ዝም ብለው እያዩት
መልካሙን ዕቃ ጥሎ ሲሄድ ያልነገሩት
የተዘነጋውን ነገር አሳስበው ያልመከሩት፣
ጥሩ ያደረጉስ መስሏቸው
ስሕተት እያዩት ማለቂያቸው።

እነማን ነበሩ በየጣቢያው የወረዱ
የጋራ ሳይሆን
የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የወደዱ፣
ወይ በፍርሃት ወይ በሞገድ
ጥልቀት በረሐ እሳት ሲነድ፣
ሳይተባበሩ ቀርተው
ከባቡር ያመለጡ ሲመስላቸው
የነገው ቀን መልካም ዕድል ይሆናቸው?

ጤናማ አመራር እንዲኖር የመከሩ
ጥረው ተጣጥረው ኃላፊነታቸውን
ለመወጣት የሞከሩ፣
በተገቢው መንገድ
አረጋግጦ እንዲጓዝ ባቡሩ
ለኃላፊው ሁሉ
ሃሳብ የለገሡት እነማን ነበሩ
በግፍ ተገፍትረው የወደቁትስ
እነማን ነበሩ።

ሄዶ ሄዶ ባቡር በመጨረሻው ያቆማል
ውንብድና ትርምሱ ሁሉ ያበቃል፣
በየመንገዱ የቀረውም ቀረ
ተሳፋሪ ሁሉ አንድም ሳይቀር ይወርዳል
አስተዋይ ሰው ከተገኘ ነገሮችን ይታዘባል
ፀሐፊም ያገኘውን ያህል ይዘግባል።

ዓለማየሁ አስፋው/ ቶሮንቶ